ቀን 30/11/99 ዓ.ም.

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች (Chapters)
በዩናይትድ ስቴትስ እና በካናዳ

ጉዳዩ፡- የስራ ጉብኝት ልዑካንንና የዝግጅት ኮሚቴ አባላትን ስለማሳወቅ

ከሁሉ አስቀድመን እኛ ከእስር የተፈታን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች፤ በሰሜን አሜሪካ የምትገኙ የድርጅቱ አባላት፣ደጋፊዎችና የኢትዮጵያ ወዳጆች፤ ከሌሎች በውጭና በአገር ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ከእስር እንድንፈታ ላደረጋችሁት ብርቱ ትግል በእስር በነበርንበት ጊዜ ይሰጠን የነበረውን የሞራል ብርታትና የህሊና እረፍት እያስታወስን ደግሞም ከተፈታን በኋላ ስለሰጣችሁን አስደናቂ ፍቅርና ስላሳያችሁን አክብሮት በድጋሚ ልባዊ ምስጋናችንን በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እናቀርባለን፡፡

እኛ ከእስር የተፈታን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረግነው ልዩ ስብሰባ ወደ ተለያዩ አህጉራት ስለሚደረገው የስራ ጉብኝት፣ስለሚካተቱት የልዑካን ቡድን አባላት፣የአቀባበል ዝግጅት ኮሚቴ አወቃቀርን በተመለከተና በሌሎችም ተያያዥነት ባላቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በሰፊው መክረን የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፈናል፡፡

1. ወደ ሰሜን አሜሪካ የሚላኩ የድርጅቱ የልዑካን ቡድን አባላትን በሚመለከት፡-

| | |
|---|---|
| 1ኛ. ኢ/ር ኃይሉ ሻውል | የልዑካን ቡድኑ መሪ |
| 2ኛ. ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ | አባል |
| 3ኛ. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ | አባል |
| 4ኛ. ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው | አባል |
| 5ኛ. ዶ/ር ኃይሉ አርአያ | አባል |
| 6ኛ. አቶ ብሩክ ከበደ | አባል እንዲሆኑ፣ |

2. የልኡካን ቡድኑ ጉብኝቱን የሚያደርግበት ጊዜ እ.ኤ.አ ከነሐሴ 20/2007 ጀምሮ እንዲሆን፣

3. የልዑካን ቡድኑን ጉብኝት አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን በሚመለከት፡-

ከዚህ በፊት ፓርቲው ችግር ሲያጋጥመው በመፍታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱና በሰሜን አሜሪካ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ አባላት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦች መሆን እንዳለባቸው በማመን፤ ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሱት ግለሰቦች የአዘጋጅ ኮሚቴው አመራር አባላት እንዲሆኑ ወስነናል፡፡

1ኛ ፐ/ር ዓለማየሁ ገ/ማርያም
2ኛ አቶ ታማኝ በየነ
3ኛ ዶ/ር ሰለሞን ዓለሙ

ስለሆነም በሰሜን አሜሪካ የምትገኙ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት ይህንኑ በመገንዘብ ስማቸው ከላይ ለተጠቀሰው የድርጅቱ የልዑካን ቡድንና የጉብኝት አስተባባሪ ኮሚቴ አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የሎጀስቲክ ድጋፍ እንድታደርጉላቸው እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር!

አቶ ኃይሉ ሻውል
ፕሬዚደንት